# ★ ዴሞክራሲያ ★

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን

**ዴሞክራሲያ ቅጽ** 36 **ቁጥር** 7 **ሐምሌ** 2003 **ዓ.ም**


## ኢሕአፓ፤ የኢትዮጵያ ህልውናና አንድነት ጥያቄ

*የሕዝብ ትግል አልፋና ኦሜጋው የሀገርን ህልውና መጠበቅ ጋር የተያያዘና የተቆራኘ ነው፡፡ መሬቱን የተነጠቀ ሕዝብ፤ ሀገር ያጣ ሕዝብ ይህ በደል እስኪወገድ ድረስ የሚታገል መሆኑን ለማወቅ የፍልስጤም ሕዝብን ሁኔታ ማጤኑ ብቻ ይበቃል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀገሩ ቀስ በቀስ ስትቆረስና ስትከፋፈል ዝም ብሎ ይቀመጣል ብሎ መጠበቅ ስህተት መሆኑን ማረጋገጥ የሚገባበት ጊዜም ደርሷል፡፡ የኢትዮጵያ ህልውናና አንድነት ለኢሕአፓ የ*40 *ዓመታት ትግል ቦታው ማዕከላዊ፤ ሚዛኑ የከባደ ከባድ፤ መደቡ መጀመሪያና መነሻ ሆኖ ቆይቷል፡፡ መስዋዕትነት የከፈልነው ለሀገራችን ህልውናና አንድነት ስንል እንጂ ለግለሰቦች የሥልጣን ጥም ወይም የባዕዳንን ፀረ ኢትዮጵያ ዓላማ እንደሌሎቹ ለማሟላት አልነበረም፤ አይደለምም ፡፡*

*ለኢትዮጵያ ሕልውናና አንድነት ሲባል ብዙ ሚሊዮን ዜጎች ሕይወታቸውን ገብረዋል፡፡ የሙሶሊኒ ፋሺሰት ጦር ኢትዮጵያን ሲወር ከሚሊዮን ያላነሱ ዜጎች ተሰውተዋል፡፡ ቀደም ብሎም በአድዋ ጦርነት ሆነ የግብፅ፤ የቱርክና የደርቡሽ ወራሪዎችን ለመጋተር ሲሉ ሺዎች ለሀገራቸው ሞተዋል፡፡ በዚያ ሁሉ መስዋዕትነት ተከብሮ የቆየው የሀገር ህልውናና አንድነት ባለፉት መቶ ዓመታት ግን ከባድ ፈተናዎች ገጥመውት በተለይም በወያኔ አጋፋሪነት ለግንጠላም ተዳርገናል፤ ሌሎችም ኢትዮጵያን ቅርጫ ሊያስገቡና ሊቦጫጭቋት--ዕድሜ ለወያኔ--አሰፍስፈው አሉ፡፡ ወያኔና የገንጣዮች መንጋ ጥርሳቸውን አግጠውና የክልል ከፍፍልን በአንቀፅ* 39 *አጅበው በኢትዮጵያ ህልውናና አንድነት ላይ ሲነሱ በሌላ በኩል ደግሞ ዜጎች ይህን አደጋ በሚገባ ተረድተውና አውቀው የመከላከል እርምጃን እየወሰዱ አለመሆናቸው ይታያል፡፡ ይባስ ብሎም እባብን በራሳቸው ላይ መጠምጠምን የመረጡ አወቅን ባዮች የሀገር ህልውናን የሚፈታተኑትን የሀገር ታዳጊዎች አስመስለው ማቅረብን ተያይዘውታል፡፡ በሀገር ዕጣና በሕዝብ ሉዓላዊነት ላይ ገበጣ ጨዋታ ወይም ንዝህላልነትን ማስፈኑ ሀገር አልባ የሚያረገን መሆኑ ላይ ምንም ጥርጥር ሊኖር ባልተገባ ነበር፡፡ ግን ወያኔን የመሰለ ተምችና ነቀዝ ያፈራች ሀገራችን ለህልውናዋ የሚዋደቁ ጀግኖችን አላፈራችም ብሎ ማሰቡ እንኳ ይቀፋል፡፡ የኢትዮጵያን ህልውናና አንድነት ለአደጋ ያጋለጡት ያለፉት መጥፎ ሥርዓቶች ለመሆናቸው ክርክር የምንገባበት አይደለም፡፡ በኤርትራ ጉዳይ የባዕዳኑ ጣልቃ ገብነት እንዳለ ሆኖ ለዚህ መንገድ የከፈተውና ቦይ የቀደደው የአፄው ሥርዓት መሆኑ ይታወቃል፡፡ ሀገር ወዳዶቹንና አርበኞቹን በአግባብ ካለመያዝ አልፎ ፌዴሬሽን የተባለውን አላግባብ በማፍረስ ፈረንጆቹ እንደሚሉት ለብሔርተኞቹ ወፍጮ ቤት*

አያሌ ኩንታል ባቄላ አቅርቧል:: በከረን፣ ኡም ሀጀር፣...ወዘተ የተወሰዱ አሰቃቂ ወታደራዊ እርምጃዎችም ሁኔታውን አባብሰው ፀረ ኢትዮጵያ ለሆኑት ኃይሎች ጠቅመዋል:: በአፄው ጊዜ የተባለሸው የነበረ ቢሆንም በተወሰነ ደረጃ ደግሞ በኃይልም በማግባባትም የተወሰዱት እርምጃዎች ግንባሮቹ እንዳያድጉ ጋሬጣ ሆነው ቆይተዋል:: ይህን ሁኔታ ደርግ የተባለው የመኮንኖች አላዋቂ ሳሚ ቡድን በተለይም ሊቀመንበር ነኝ ይል የነበረው ማፈሪያ ነፍሰ ገዳይ ሳይውል ሳያድር አበላሽቶና አበሻቅጦ ለግንባሮቹ ዕድገትና መጠናከር ከፍተኛ አስተዋፅዖንም እድርጓል:: ዛሬ አንዳንድ የታሪክ በራዦች እንደሚወሽክቱት የኤርትራን ትግል በመቀስቀስም ሆነ በመርዳት ኢሕአፓ ምንም ሚና አልነበረውም:: የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ መሬት ለአራሹ-ብሎ በማያወላዳ መልክ ለሥር ነቀል ለውጥ ከመነሳቱ ከአምስት ዓመት በፊትና ኢሕአፓ ከመመስረቱ 14 ዓመት በፊት የኤርትራ ነፃ አውጪ ግንባር ጀብሐ ተመስርቶ የትጥቅ ትግል ጀምሮ እንደነበር ታሪክ የሚያውቀው ነው:: ኢሕአፓ እንደ ድርጅት የብሔረሰብን አጠቃላይ ችግር ከእኩልነት አንፃር የሀገር አንድነትን ከዴሞክራሲ አያይዞ ለማስከበር በመሻት በጊዜው በነበረው ርዕዮተ ዓለም መሠረት የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብትን ቢያውቅም ይህ አቅዋሙ የሀገራችንን ሕዝብ አንድነት ያረጋግጣል በሚል ተስፋና ዕምነት ላይ በመመሥረት ነበር:: የሀገር ግንጠላንና ጠባብ ብሔረተኞችን የመደገፍ አቅዋም ኢሕአፓ ቢኖረው ኖሮ የኤርትራ ግንባሮች ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ናት ሲሉ፣ ወያኔ በ1967 ጦማሩ ወይም ማኒፌስቶው ሁሉም ብሔረሰቦች ተገንጥለው የራሳቸውን ነፃ መንግሥት ያቋቁሙ ሲል፣ ዚያድ ባሬ ሲሶ በላይ የኢትዮጵያን ግዛት ምዕራብ ሶማሊያ ነው ሲል አዎን እሺ ብሎ ተቀብሎ በተገኘ ነበር:: ኢሕአፓ ግን ለኢትዮጵያ የማይበጀውን ዕቅድና አቅዋም በመቃወሙ በወያኔም በሻዕቢያም ተወግቷል:: ጥቃት ደርሶበታል:: ለመሆኑ ያኔ ከኢሕአፓ ጎን የቆሙ፣ ጠባብነትንና ግንጠላን እንዲሁም የታሪክ ብረዛን የተቃወሙ፣ የሕዝብና የሀገርን አንድነት ለማስከበር እንደ ኢሕአፓ መስዋዕት የሆኑ ሌሎች እነማን ነበሩ?

የደርግ አገዛዝ ሽክላ ሳህን መሸጫ ሱቅ ውስጥ ገብቶ እንደደነበረ በሬ ግራ ቀኙን ሲያተራምስ፣ ሲሰባብርና ሲፈጅ፣ ለግንባሮቹ ሾክ ሆነው የነበሩትንም እነ ጄኔራል አማን አንዶምን ገድሎ፣ በአሥመራ ከተማ በሽብር ወጣቶችን አሳንቆና አስደንብሮ፣ ብሎም ሕብረ ብሔራዊ የሆኑትን እነ ኢሕአፓ ዓይነቶቹን በትውልድ ደረጃ ጨፍጭፎ ለግንባሮቹ ጠቀመ:: የራሱን ጦር አዛዦችንም እየረሸነ፣ ጦሩን በደህንነት ሠራተኞች፣ ዘባራቂ ካድሬዎችና ኮሚሳሮች እያዋከበ አዳከመ:: ግንጠላውን አመቻቸ:: የእናት ሀገር ጥሪ ብሎ ስንቱን ዜጋ አሰቃየ፣ አስጨረሰ:: ችሎታ ቢሶች አመራርና አዛዥ ተብለው፣ ተመክሮ ያላቸው ተገልለው፣ በውሱንና ጠባብ የግለሰብ ፍፁም ሥልጣን ዙሪያ የሀገር ጥቅምና መሠረታዊ ፍላጎት ተጠንጥኖ፣ ግብዙ ኮለኔል በዕብሪት ሀገርን ለአደጋ አሳልፎ ሰጥቶ በድፍረት ሊሰዋ ቀርቶ በፍርሀት ፈረጠጠ:: ማን ይወቀስ የተሳሳተ፣ ማን ይከሰስ ያጠፋ ሆኖ ሳለ ሥልጣን ይዘው የሀገርን አንድነት ያናጉና ህልውናዋንም ሊሰርዙ የተነሱት አገዛዞች እያሉ (ደርግም ወያኔም) ኢሕአፓን ለመወንጀልና አስገነጠለ፣...ወዘተ ብለው ሊከሱ የሚጥሩት ሁሉ ከታሪክ የተጣሉና ሐቅን የጠሉ መሆናቸውን እናያለን:: ለሀገር አንድነት ብለው በየጦር ግንባሩ የወደቁት ሀገር ወዳድ ዜጎች ሁሉ የነዚህ ከሀዲ አገዛዞች ሰለባ መሆናቸው

በአሉታዊ የሚያስመዘግባቸው ሊሆንም አይገባም:: አገዛዙ ሕዝብን በጨረሰ፣ ሰለባ የሆነውን ተጠቂውን አለቀ ሳይሆን በግልባጩ አስጨረሰ ብለው የሚከሱ አረመኔውን አንቱ ብለው ስሙን ለማደስ የሚጥሩ፤ ዛሬም በመሀላችንና በሕብረተሰቡ ዘንድ የጭራቁ ሥርዓት አዳናቂዎችና ወንጀለኞች አሉ:: በ1983 ሥልጣን ይዞ የኤርትራን ግንጠላ ያመቻቸው ወያኔ ሆኖ ሳለ ይህን ለመካድ የሚጥሩ ሀሰተኞች ናቸው:: አንቀፅ 39ን ሕግ ያለውና ሀገሪቷን በክልል የሸነሸነው ኢሕአፓ ሳይሆን ወያኔ ነው:: ይህንንም መዘንጋት ከህቅ ጋር መጣላት ነው::

ሀገራችን ኢትዮጵያ በሕዝብ እኩልነት መረጋገጥ መስከ ዛሬ ችግሮቿ ተባብሰዋል እንጂ አልቀነሱም:: ይህ ችግር የኢትዮጵያ ተራማጅ ኃይሎች፤ ተማሪዎች ወይም ኢሕአፓ የፈጠሩት ችግር አልነበረም:: እነዚህ ሁሉ በኢትዮጵያ የፖለቲካ መስክ ገና ብቅ ሳይሉና ሚዛን ሳይዙ የኤርትራ ትግል፣ በኦጋዴን ጦርነት፣ በባሌ የነዋቆ ጎቱ አመፅ፣ የሜጫ ቱለማ እንቅስቃሴ፣ ...ወዘተ በሀገራችን ተከስተው ነበር:: ተራማጁ ክፍል ለችግሮቹ መፍትሔ ለመስጠት ጣረ፣ ሞከረ እንጂ የሌለ ችግርን ቆስቁሶ ደስ ያለውን ሕዝብ የለም አዝነሃል ብሎ አሳምኖ አላሳመፀም:: ትግል የብሶት ውጤት ነው፤ አለምክንያት ዜጎች አያምፁም፤ ራሳቸውንም ለሞትና መስዋዕትነት አያዘጋጁም:: በመራራ የትግል ሂደት ያላለፉና ያልተፈተኑ ሁሌም ትግል ቀላልና ዜጎች ሳያስቡና ሳያወጡ ሳያወርዱ የሚያምፁ ይመስላቸዋል--ይህ ግን ከሐቅ የራቀ፣ መሰረተ ቢስ ድምዳሜ ወይም ግንዛቤ ነው:: በደል ባለበት ግን ዜጎች ያምፃሉ--ይህን ትግላቸውን ሌላ አቅጣጫ የሚያስይዙ መኖራቸው ወይም መነሳታቸው ግን የበደላቸውን መኖር የሚለውጥ አይደለም:: በመሆኑም እኩልነት ባልነበረበት የአፄው ሥርዓት ጊዜ ሕዝብ በየቦታው ማመፁና እኩልነትን መጠየቁ ተገቢና አይቀሬም ነበር ማለት ይቻላል:: የኢትዮጵያን ህልውናና አንድነት ለማስጠበቅ ስንታገልና የነገይቷን ኢትዮጵያ አንድነት ለማረጋገጥ ስንታገል በቅድሚያ መታወቅ ያለበት ጉዳይ ይህ ትግልና ግብ ያለፈውን የጭቆና ዘመን ለመመለስ ሊሆን እንደማይችል ነው:: ዛሬ በወያኔም ሆነ በመሰሎቹ ፊሊጥ ተብሎ የተጧጧፈው ፀረ ቴዎድሮስና ፀረ ምኒልክ ዘመቻ በመሠረቱ ታሪክ አለማወቅን የሚያሳይ ከመሆኑ ሌላ የዛሬን የራስን ወንጀል ለመደበቅ መሆኑ ግልፅ ነው:: በኢትዮጵያም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ (የጣሊያንና የጀርመንን የአንድነት ጉዞ በጋሪባልዲና ቢስማርክ ሥር ያጤኗል) የሀገር አንድነት ሂደት የኃይል እርምጃዎችን ያቀፈ እንደነበር ግልፅ ነው:: በዚያን በሩቅ ዘመን የነበሩ መሪዎች/አፄዎች በዛሬ ዘመን ዴሞክራሲያዊ ፅንሰ ሀሳብ መሠረት የሚጠበቅ ሊሆን ባልተገባ ነበር:: ይልቁንስ ዛሬ የዚያን ጊዜ ዘዴና መንገድ በመጠቀም ሕዝብን የሚጨፈጭፉት ዘመናዊ ነን ባዮች፣ ነፃ አውጪ ነን ባዮች ተጠያቂዎች ናቸው:: ይህን አቢይ ጉዳይ በተመለከተ ዘጠኝ ዓመት በፊት በወጣ የዴሞክራሲያ ዕትም የሚከተለውን አስፍረን እንደነበር መጥቀሱ ይጠቅማል--

> *"በታሪክ ሂደት ሀገሮች ሲገነቡ ወይም በተለምዶ አነጋገር ሲቀኑ ዴሞክራሲንና የሕዝብን ፍላጎት ተመስርተው አይደለም:: በዓለም ውስጥ ዛሬ በሀገርነት እየታወቁ ያሉትን ስናይ ይህንኑ እንረዳለን:: የሀገር ግንባታው ሂደት በያለበት ጠመዝማዛና ሰላምን ሳይሆን ጦርነትን ያስቀደመ ነበር:: በሂደቱ የጠፋው ሕይወት ቢያሳዝነንም የዘመኑ መሪዎች ዛሬም እንኳን ለእኛም አስቸግሮ ያለውን መቻቻልና*

*ዴሞክራሲያዊነት ለምን ያኔ አላንፀባረቁም ብሎ መወንጀል ፍፁም ተገቢ አይሆንም:: ሕዝቦች በጦርነት አልፈው በጋራ መኖር ጀምረው መቶ ብቻ ሳይሆን በዙ መቶዎችና ሺ ዓመታት ካለፈ በኋላ ግን የታሪክን ጎማ ወደ ኋላ በመጎተት ቂምና ቁርሾን በማራገብ ከዘመናት በፊት ለፈሰሰ ደም የዛሬውን ትውልድ ተጠያቂ በማድረግ ክፍፍልን መቀስቀስና ማንገሱ የሚደገፍ ሳይሆን የሚወገዝ ነው:: የነገ ኢትዮጵያን ዕድል ልንወስን ስንነሳም ሞተው ዘመን ያስቆጠሩ የዘመናቸው ነፀብራቅ የሆኑትን አፄዎች በዛሬ መነፅር በመመርመርና በማውገዝ ስንት መከራን በጋራ ያሳለፈን አንድነትና ኢትዮጵያዊነት መሠረዝ ፍፁም የሚቻልና የሚገባም አይደለም:: ..(ሁሉም) ሕዝብ የኢትዮጵያ ታሪክ ሙሉ ባለቤት ነው እንጂ ኢትዮጵያዊነቱን ለማስረገጥ ድርድርን አይፈልግም:: በኢትዮጵያዊነታችን ላይ ገደብ ሊጥሉብን፤ ግደፈት ሊፈጥሩብን፤ ሊያውገረግሩብንና ማንነታችንንም ሊክዱ የተነሱትን ሥርዓቶች የምንታገላቸውም በኢትዮጵያዊነታችን ላይ ካለን ጠንካራ እምነት የተነሳ ነው:: ኢትዮጵያዊነታችንን ሲክዱ አዎን ብለን መቀበል ሆነ መገንጠልን ማቀንቀን ደግሞ ስህተት መሆኑ ሊታመንበት ይገባል::”*

የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነትን እንደሚመርጥ ደግሞ ደጋግሞ አሳይቷል፡፡ በየካቲት አብዮት ጊዜ በጋራ በመነሳት የብሔረሰብና የሃይማኖት ልዩነትና ጭቆና እንዲወገድና ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ እንድትመሠረት በመጠየቅ ለአንድነቱና ለሀገሩ ያለውን ፍቅር አሳይቷል፡፡ በ1997 ዓ.ም ደግሞ አንዳንዶች ኢትዮጵያን በሚመለከት ምርጫ አትግባ፤ ኢትዮጵያዊ አይደለህም ብለው ሲቀሰቅሱትና ሲጮኹበት ወግዱ ብሎ ለቅንጅትም ለህብረትም ድምፁን ሰጥቷል፡፡ ህብረ ብሔራዊውን ትግልና ድርጅቶች በ1966 ሆነ በ1997 በመደገፍ ሕዝብ ፍላጎቱ አንድነትና ዴሞክራሲ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ የኢትዮጵያ አንድነት በዴሞክራሲና በእኩልነት ላይ መመሥረት አለበት እንዳልነው ሁሉ፤ ወደ አለፉት የጭቆና ሥርዓቶች መመለስ አይገባም አይቻልምም እንዳልነው ሁሉ እኩልነትና መብት በሌላ በኩል በመገንጠልና ሕዝብን ከፋፍሎ በማናከስ ከቶም የሚገኝ አለመሆኑን አጠብቀንና ጫና ሰጥተን ደግመን ደጋግመን አቅርበናል፡፡ ይህን በተመለከተ በግንቦት 1994 ዴሞክራሲያ ዕትም አስፍረን የነበረው ዛሬም ሙሉ በሙሉ ሁኔታውን ገላጭ ሐቅ ነው--

*“የንበረ ብሔራዊው ወይም ኢትዮጵያዊው ጎራ የነበረውን ቀና የአንድነት መንፈስና ለዚህም ጥሩ መሰረት ለመጣል ያስችላል ብሎ ያቀረበውንም መፍትሄ ጠባቦቹ በፅንፉ ብቻ አጉልተው መገንጠል ወይም ሞት የሚለውን መፈክር በማንሳት <u>የራስን ዕድል በራስ መወሰን የተባለውን የሥልጣን ማዕከላዊነትን በማስወገድና ሕዝብን የራስ አስተዳደርና ዴሞክራሲያዊ መብትን በማጎናፀፍ ደረጃም ተግባራዊ ሊሆን መቻሉ ተዘንግቶ መገንጠልን ማፅደቅ ብቻ እንደሆነ በጠባቦች ተተረጎመ</u> :: የራስን ዕድል በራስ መወሰን በግድ መገንጠልን ያዘለ አይደለም የሚለው የገባቸው የኤርትራ እንቅስቃሴዎች ደግሞ የኢትዮጵያ ቅኝ ተገዢ ነን የምንለውን ተቀበሉልንና እንደ ማንኛውም ቅኝ ግዛት በግድ ነፃ የመሆን*

*መብታችን ይከበርልን አሉ ። ኢትዮጵያን በጠላትነት በጥቅሉ በመፈረጃቸውም የጠባብ ብሔረርተኞች ደጋፊና ፈጣሪም ሆነው በኢትዮጵያዊ ድርጅቶች ላይ በጋራ ተነሱየ ። ኢሕአፓ የዚሁ ሴራ ዋነኛ ተጠቂ እንደነበር ታሪክ የመዘገበው ሐቅ ነው።"*

ጥበትና ግንጠላን ማቀንቀን ከመሠረቱ የሀገርን ህልወናና አንድነት ተፃራሪ ነው። በመብት ረገጣ ላይ የሚመሠረት አንድነት የፀና አለመሆኑ ግልፅ ሲሆን ለመብት ረገጣው መፍትሔው ደግሞ መለያየት መገንጣጠል ነው ብሎ ወይም ወያኔ ይል እንደነበረው የኢትዮጵያ ሕዝብ አብሮ ለመኖር መቼም አይችልምና ይከፋፈል፣ ይለያይ ብሎ መደምደም ደግሞ ሀገርን አጥፊ ስህተት ነው። ጠባብ ብሔረተኛነት ራሱ ጎጂ ዝንፈትና የትምክህትም ሌላ መጥፎ ገፅታ ነው ስንል ቀደምም የገለፅነው ነው። በቅድሚያ ማንም ሳይመርጣቸውና ሳይመድባቸው የብሔረሰባችን <u>ብቸኛ</u> ተጠሪ ነን ብለው ራሳቸውን በመሰየም ሕዝብን ጠልፈው ሌሎችን ውጡልን፣ ከሕዝባችን ራቁ ማለትን ያስቀድማሉ። ይህን ዝም ብሎ መቀበል ወይም ታሪክን በካደ ድርቅና ሕዝብን ኢትዮጵያዊ አይደለም ብለው ባዕድ ሲያደርጉ መቀበል ሀገርን ለጥፋት አሳልፎ መስጠት ነው። ሕዝብ ተበደልኩና ተጨቆንኩ ብሎ መነሳትና ጥቂቶች የሕዝብን ብሶትና ጩኸት ቀምተው ወደ ፅንፍ በመውሰድ ባዕድ ነን፣ ኢትዮጵያዊ አይደለንም፣ መገንጠል አለብን፣ ...ወዘተ ማለት አንድ አይደሉም። ዛሬም ቢሆን ሊካድ የማይችለው ሐቅ ሕዝብ ጭቆና እንደሚደርስበት ነው። ወያኔ ያሰፈነው ዘረኛ ሥርዓት ብዙሃኑን በብሔረሰብና በሃይማኖትም ደረጃ ይበድላል፣ ይጨቁናል-- ይህም መወገድ ማብቃት አለበት። እንዴትና በምን ዓይነት የሚለው ግን ዛሬም አከራካሪ ሆኖ በጋሬጣነት ተዘርግቷል። በኢትዮጵያዊነት መደራጀቱ አሁንም ከባድ የሆነባቸው ወይም የማይታሰብ ነው የሚሉ፣ ይባስ ብለውም ኢትዮጵያ ካልፈራረሰች መብታችን ሊከበር አይችልም የሚሉትን ከጎጂና የተሳሳተ ጎዳናቸው ለመመለስ መጣርና አሊያም መቋቋም አስፈላጊ መሆኑ ግልፅ ነው።

የኢትዮጵያን ውስጣዊ ችግሮች የሚያባብሱና ሀገራችንን ከፋፍለው ሊገዙ ወይም ሊያጠፉም የሚመኙ ባዕዳን ኃይሎች ዛሬም እንደበፊቱ አሉ ። በተለይም ኢትዮጵያን እየሸጠላቸው ያለውን ከሀዲ ቡድን በመደገፍ የሕዝብን ስቃይና መከራ እያባባሱ ናቸው። እነዚህ ክፍሎች ሁሉ በስውርና በተወሰነ ደረጃ በይፋም ኢትዮጵያን በሃይማኖትም ሆነ በብሔረሰብ ለመከፋፈልና ከተቻለም ሀገሪቷን ለመበጣጠስ ያቅማቸውን እየሰሩና ነጋ ጠባም እያሴሩ ናቸው። የሕዝብን የጋራ ታሪክ እየሰረዙና እያክቸለቸሉ፣ ልዩነትን በወያኔ ረዳትነት እያራገቡ፣ ሕዝብን እርስ በርሱ ነጥለውና አቃርነው የጋራ ከንድ እያሳጡ ሀገሪቷን ለባዕድ ብዝበዛና ወረራ አጋልጠዋታል። የኢትዮጵያ ህልውና ዛሬ በአስከፊና አስፈሪ አደጋ ላይ ነው። የአንድነት ኃይሎች ህልውናና ትብብር ደብዝዞ በሚያሳዝን ደረጃና ሁኔታ የፖለቲካው መድረክ በጠባቦች (ማለትም በወያኔና ተቃርነነዋል በሚሉ ግን መሰሎቹ) መያዙ ሳይበቃ ከሕዝብ ጎን ቆመናል የሚሉ አንዳንድ ክፍሎችም ተደናግረው የሀገርን ህልውና የሚፃረሩትን ሲደግፉ ማየትም ጀምረናል። ከ1983 በፊት ይሰማ የነበረው የሕዝበ-ውሳኔ (ሬፌራንደም) ጫጫታም ዛሬ የገደል ማዎች ያገኘ ይመስላል። ሕዝበ-ውሳኔ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሰፍኖ የሚመለከተውንም ሕዝብ ሁሉ አሳትፎ

ከማንም ኃይል ተፅዕኖ ነፃ በሆነ መንገድ ይካሄዳል እንጂ በኤርትራ የታየው የአንድ ኃይል ቁጥጥርና "ባርነት ወይስ ነፃነት"--ምረጥ!--ማለቱ ህጋዊና ዴሞክራሲያዊ ሂደት ሊሆን አይችልም። ሕዝበ-ውሳኔ አይደለም--ይህ ደግሞ ዜጎች ነቅተው ባለበት ነገ ይደገማል ብሎ ማለሙ ሞኝነት ነው።  የሕዝብ መብትና ዴሞክራሲ ካልተከበረ አንድነት ተሸርሽሮ የሀገር ህልውና ለአደጋ መጋለጡ አይቀርም እንዳልነው ሁሉ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ክዶና አውግዞ የሚፈለግም መፍትሄ የውሀ ሽታ ሆኖ የሚቀር ነው። የመገንጠሉ ጥቅም ዜሮ መሆኑን ደግሞ ከቅርብ ተመክሮ ያየነው ሲሆን የተገነጠለችው ኤርትራ መሪ ደቡብ ሱዳንን መገንጠል አይጠቅማችሁም ብሎ መምከሩን ሌሎች መገንጠል ወይም ሞት የሚሉ ክፍሎች ሊያጤኑት የሚገባ ነው - ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው ይባል የለ!

ድምዳሜያችንና ጥሪያችን ቀደም ካቀረብነው የተለየ አይደለም።

> *"ኢሕአፓ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች ለአንዴም ለሁሌም የመገንጠልን አማራጭነት ውድቅ አድርገው የዴሞክራሲያዊ አንድነትን አማራጭ የለሽነት እንዲቀበሉና ለዚህም ተባብረው እንዲታገሉ ጥሪ ያደርጋል ። ኢትዮጵያዊነት ደግሞ የሁሉም ትግልና መስዋዕትነት ውጤት በመሆኑ ማንም ቢሆን ማን ይህንን መለያውን ሊቀማ ካለመቻሉ ሌላ ሊጠራጠረው የሚገባም ጉዳይ አለመሆኑም ሊታመንበት ይገባል። የብሔረሰቦች ወግ፣ ባህል፣ ታሪክና ቋንቋዎች ተከብረው ለሀገራዊ አንድነታችን ጠቃሚ የሆኑ ቅርሶቻችንና እሴቶቻችን መሆናቸውም ታምኖበት ሁላችንንም በእኩልነት ያቀፈች ታላቅ ሀገር፣ የሁሉም ሕዝብዋ የጋራ የሆነች ሀገርን በጋራ ልናጠናክር እንችላለን ብሎ ኢሕአፓ ያምናል። ለዚህም ልክ እንደበፊቱ ይህን ቅዱስ ዓላማችንን ከሚፃረሩ ፅንፎች መራቅና በተከሰቱበትም መታገል ይኖርብናል። ለእኩልነትና ለመብት መከበር መቆም ተገቢና ፍትሃዊ ነው። ለሀገራችን ኢትዮጵያ በጋራ መታገልና ዜግነታችንንም ማስጠበቅ ደግሞ ግዴጃችን ነው። በዚህም መልክ ሲታይ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት በዴሞክራሲ ለም ማሳ ላይ ጸድቆ እውን እንዲሆን በመታገል የወያኔን ዘረኛና ከፋፋይ አገዛዝ ማስወገድ የሁላችንም ተቀዳሚና ዋና ተልዕኮ ሊሆን ይገባዋል ሲል ኢሕአፓ ያሳስባል።" (ዴሞክራሲያ፣ ግንቦት 1994)*

*የኢትዮጵያን አንድነትና ህልውና ለመጠበቅ በጋራ እንታገል !!*